
# የጉዞ ገጠመኞች



This book came about without much planning. A bunch of literacy coordinators who run non-formal, Mother Tongue literacy programs for adults in Gamo, Konso, Dirashe, Shekacho, Daasenech, Suri, and Diizin languages, got together in Addis Ababa to learn about how to produce small booklets in their own languages.

But before they got to the task they all had their travel stories to share. The stories were so exciting that we decided to make a book out of them. So the coordinators wrote down their stories in the evenings, and by the end of the time together there was a pile of adventures to type, edit, and publish.

May you enjoy this small piece of literature, and may it encourage you, too, to contemplate on your own, unique everyday experiences, write them down, create stories and become a story teller and a literature producer.

Addis Ababa, July 2014

*Aija Katriina Ahlberg*

# የጉዞ ገጠመኞች

| | |
|---|---|
| ደራሲያን፡ | የመሠረተ ትምህርት አስተባባሪዎች ስልጠና ተካፋዮች፥ አዲስ አበባ 11/09-15/09/2006 ዓ.ም. |
| የአርትዖት ሥራ፡ | የኋላሸት ደሳለኝ |
| ሰዓሊ፡ | ሰናይት ወርቁ ማሞ |


አሳታሚ፡ ኤስ አይ ኤል ኢትዮጵያ
መሠረተ ትምህርት ክፍል
አዲስ አበባ፤ ሐምሌ 2006 ዓ.ም.
1ኛ የሙከራ እትም

## መውጫ

ነጭናጫው ሾፌር ......... 1

ተስፋ አልቆረጥንም ......... 8

ከቱም እስከ አዲስ አበባ የ4 ቀን ጉዞ ......... 14

ሞገደኛው ሾፌር ......... 18

ሰው ቃሉን አይመስልም ......... 21


ከደራሼ እስከ አዲስ አበባ ......... 25

መብት ረጋጩ ሾፌር ......... 28

የቲኬቱ መዘዝ ......... 36

# ነጭናጫው ሾፌር

በአዲስ አበባ ከተማ ለኤስ አይ ኤል (SIL) የመሰረተ ትምህርት አስተባባሪዎች የሚሰጥ ስልጠና እንዳለ ከሰማሁ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል። ስለ ስልጠናው ሳስብ ደስታ ይሰማኛል። አዲስ አበባንም በአይነ-ህሊናዬ እያየሁ «አወይ አዲስ አበባ!» እላለሁ።



እንግዲህ የተቀጠረለት ቀን መድረሱ አይቀርምና ጊዜው ደረሰ። ከአርባ ምንጭ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ የአውቶቡስ ቲኬት የሚገዛው ከጉዞው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ነው። ስለ ጉዟችን ከውድ ባለበቴ ጋር ከተማከረን በኋላ እኔ የአውቶቡስ ቲኬት እንድገዛ ተስማማን። በዚህ

መሰረት ግንቦት 7/2006 ዓ/ም በማለዳ ተነሳሁና ጠደፍ ጠደፍ እያልኩ ከጧቱ 2፡00 ሰዓት ላይ መናኸሪያ ደረስኩ። ቲኬት ሽያጭው ቢሮውን እየከፈተ «ማኛው! ደህና ነህ?» አለ። እኔም ሰላምታውን ከመልስኩት በኋላ «ማኛው» የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ማሰላሰል ጀመርኩ። በርግጥ ቃሉን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጥቂት ሰዎች በከተማችን ውስጥ ሲጠቀሙበት እሰማለሁ፤ ትርጉሙን ግን አላውቀውም። ድንገት «አዲስ አበባ ልትሄድ ነው?» አለኝ ቲኬት ቆራጩ። እኔም «አዎ» አልኩት፤ ከሄድኩበት ሃሳብ እየተመለስኩ።

«ስንተኛው የወንበር ቁጥር ይመችሃል? እስከ አራት ያለውን ቦታ ሰዎች ስልክ ደውለው እንዲያዝላቸው አድርገዋል» አለኝ። እኔም «ችግር የለም! ከሾፌሩ በስተ ጀርባ አይሁን እንጂ እኔና ባለቤቴ ጎን ለጎን የምንቀመጥበትን ሁለት መቀመጫዎች ካገኘህልኝ ይመቸኛል» አልኩት። «ባለቤቴ» የሚለውን ቃል ሲሰማ፣ «ባለቤትህ ደህና ነች?» አለኝ። እኔም «አዎ ሰላም ነች» አልኩት። እሱም «አትታይም አሃሃ!» ብሎ እየሳቀ በወንበር ቁጥር አምስት እና ስድስት ላይ መቀመጥ የሚያስችለንን ቲኬት ቆርጦ ሰጠኝ። እኔም ሶስት መቶ ብሬን ከፍዬ ወደ ሥራዬ ሄድኩኝ።

ረቡዕ ለመጓዝ ማክሰኞ ምሽት ሻንጣችን ካዘጋጀን በኋላ ተኛን። ባለቤቴ ሌሊት እንዲቀሰቅሰን ሞልታ ያስቀመጠችው የሰዐት አላርም (ደወል) ከሌሊቱ አስር ሰዐት ከሃያ ሲሆን ጮኸ፤ እኔም ደንግጬ ተነሳሁና "ውይ! ሰዓቱ ከመቼው ደረሰ አልኩኝ" በውስጤ እየተበሳጨሁ። ባለቤቴ ተነስታ መብራት ካበራች ከአምስት ደቂቃ በኋላ እንደምንም

ብዬ ተነሳሁ። ልብሳችን ለባብሰን፣ ፀሎታችንን አደራርሰን፥ ሻንጣችን ያዝንና ቤታችን ቆልፈን ወደ መናኸሪያ ጉዟችንን ጀመርን። ምን እንደሆነ አላውቅም፣ ውስጤን ፍርሃት ፍርሃት አለኝ። ምናልባት ወደ መናኸሪያ ስንሄድ ሊያጋጥሙን የሚችሉትን ዘራፊዎች እያሰብኩ ሊሆን ይችላል፤ ወይም በተበላሸ አስፓልት ላይ ቁርሳችንን ሳንበላ እስከ ሆሳእና ድረስ የምናደርገውን ጉዞ ሳስብ ይሆናል ፍርሃት ፍርሃት ያለኝ። እናም ሳላስበው «አወይ! የአዲስ አበባ ጉዞ!» አልኩ በውስጤ።

ይህ ሁሉ ቢያሳስብኝም መናኸሪያ በሰላም ደረስን። ወደ አውቶብሱ ውስጥ ስንዘልቅ የቆረጥነው የመቀመጫ ቁጥር የሚገኘው እንዳሰብነው ሳይሆን በማንፈልገው በሾፌሩ ጀርባ ሆኖ ተገኘ። ምንም እንኳ ከሾፌሩ ጀርባ መቀመጥ ባልወድም የቆረጥነው የወንበር ቁጥር የሚገኘው በሾፌሩ ጀርባ ነውና ተቀመጥን። ሆኖም ባለቤቴ ቦታውን ወዳዋለችና ተረጋግተን ተቀመጠን። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ኋላዬ ዞር ስል ከአንድ የማወቀው ወዳጄ ጋር አይን ለአይን ተጋጩንና በአየር ላይ ሰላምታ ተለዋወጥን። የወዳጄ ቁመት ረጅም ስለነበረ የተቀመጠበት መሃል ወንበር ለረጃጅም እግሮቹ ምቹ አልሆኑለትም። ስለዚህ ከእኛ አጠገብ ከተቀመጠው መንገደኛ ጋር ቦታ ተቀያይሮ እኛ ወዳለንበት መጣ።

ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት አከባቢ ሾፌሩ ወደ መኪናው ገባ። በሾፌሩ በኩል ያለው በር ባግባቡ ስለማይዘጋ ሾፌሩ በረጅም ገመድ እየጠመጠመ ሲያስር አየንና ሁላችንም በጣም ተገረምን። የመኪናውን ሞተር አስነስቶ መንዳት ጀመረ። ረዳቶቹ «አምስት ሰዎች ይጎድላሉ፥ ትንሽ እንጠብቅ» ቢሉም ሾፌሩ ሊሰማቸው አልቻለም።

የአውቶብሱ የመንገደኞች መግቢያ በር አልተዘጋም። መናኸሪያ መውጫ በር አከባቢ ስንደርስ አንድ ሰው ተንጠልጥሎ ገባ። ረዳቶቹን መስማት ያልቻለው ሾፌር ከመናኸሪያው እየነዳ ወጣ። ሾፌሩ በትንሽ ነገር ይነጫነጫል። እኔም በውስጤ እየተገረምኩ «ይህን ሰው ምን ነካው? ለምን ይነጫነጫል? ሲያዩት ወጣት አይመስልም፤ ትልቅ ሰው ነው» አልኩ። ወደ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ትልቁ ካምፓስ በር ስንደርስ ቲኬት የቆረጡም ያልቆረጡም ሰዎች ተደባልቀው የተሳፋሪው ቁጥር ከአውቶብሱ የወንበር ቁጥር በላይ ሆኗል። ሾፌሩ ከወንበር በላይ ትርፍ መጫኑ ምንም ያሳሰበው አይመስልም። መንዳቱን ቀጠለ።

ላንቴ ከተማ የደረስነው በማለዳ ነበር። በዛ ንጋት ላይ ማንጎ የሚሸጡ ልጆች የላንቴን መንገድ መለስተኛ ገበያ አስመስለውት ነበር። ሾፌሩም መኪናውን ጥግ አስይዞ አቆመ። አቤት ግርግር! አቤት ጩኸት! አቤት የፌስታል ነጋዴ! አቤት የማንጎ ነጋዴ! አብዛኞቹ ወደ መኪናው በር ለመግባት ይታገሉ ነበር። ሌሎች ደግሞ የሚሸጡትን የየራሳቸውን ዕቃ በመስታዋት ለማስገባት እየታገሉ፥ «የእኔን ግዛ! የእኔን ግዛ!» እያሉ ይጮሁ ነበር። እኔም “ምን አለ ቪዲዮ ካሜራ ቢኖረኝና ይህን ትዕይንት ቀርጬ ሌሎች ሰዎች ባሳይ” ብዬ አሰብኩ። ያ ጨቅጫቃ ሾፌር መንገደኞች የሚገዙትን ሳይጨርሱ፣ የሚሸጡትም ልጆች ከመኪናው ሳይወርዱ፥ የመኪናውም በር ሳይዘጋ መኪናውን ማንቀሳቀስ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ልጆቹ «ወራጅ! አውርደን!» እያሉ ሲጮሁ የግዱን አቆመና አወረዳቸው። ከዚያም ጉዟችንን ቀጠለን።

አጠገቤ ከተቀመጠው ወዳጄና ከባለቤቴ ጋር ልዩ ልዩ ጉዳዮችን እያነሳን ጉዟችንን ተያያዝነው። አንዳንዴ ስለ ቤተክርስቲያን ሁኔታ አንስተን እናወራለን፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ የአርባ ምንጭ ወላይታ መንገድ ሥራ ከተጀመረ ሳይጠናቀቅ ከሰባት ዓመት በላይ መቆየቱን አንስተን በመገረም እንጨዋወታለን፤ ስለ መንግስትም አንስተን እየተጫወትን ጉዟችንን ቀጠለን። ሾፌሩ የከፈተው ዘፈን መኪናውን የመንገደኞች አውቶቡስ ሳይሆን የመጠጥ ቤት አስመስሎታል። ከዚህ የተነሳ አንዳችን ለሌላው የምናወራው ወሬ በቅጡ ስለማይሰማ ጆሯችንን ወደሚያወራው ሰው ጠጋ እያደረግን ነበር ሃሳብ የምንለዋወጠው።

ወላይታ ዞን ገብተን ሶዶ ከተማ ልንደርስ ጥቂት ኪሎሜትር ሲቀረን ከፊታችን ዘና ብሎ የቆመ ትራፊክ ፖሊስ መኪናችን እንዲቆም በምልክት አዘዘ። ትርፍ ሰው መጫኑን የተረዳው የትራፊክ ፖሊስ የሾፈሩን መንጃ ፈቃድ ወስዶ ከመኪናው ወደፊት ራቅ ብሎ የክስ ወረቀቱን ለመጻፍ መዘጋጀት ጀመረ። ሾፌሩ እየተጨቃጨ፥ ሁለቱ ረዳቶች ደግሞ ከፖሊሱ ኋላ ኋላ እየተከተሉ ቅጣት እንዳይጻፍባቸው ይለምናሉ። በዚህ መሃል ሰዎች ለሽንት ሲወርዱ አይቼ እኔም በዚያ አጋጣሚ ተንፈስ ልበል ብዬ ወርድኩኝ። ከብዙ ጭቅጭቅና ልመና በኋላ ፖሊሱ መንጃ ፈቃዱን ለሾፌሩ እየመለሰ «በእውነት ልንገሮት! እንደ እርሶ ያለ ነዝናዛ እና ጨቅጫቃ ሰው አይቼ አላውቅም» አለ። እኔም በውስጤ «እውነትህን ነው!» አልኩ።

ይኸው ጨቅጫቃ ሾፌር ለሽንት የተበተኑ መንገደኞች ተጠቃለው ወደ መኪናው ሳይገቡ እንደልማዱ መኪናውን ማንቀሳቀስ ጀመረ።

መንገደኞችም እንደምንም እየተሯሯጡ ገቡ። እኛም አሁን ደከምከም እያለን ነው። ስለዚህ ትንሽ እንጫወትና ሳናስበው እንቅልፍ ይዞን ጭልጥ ይላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመካከላችን ዝምታ ይሰፍናል። በዚህ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ ሁኔታ ወደ ሀሳቤ ይመጣል። "መጥፎ ሽታው፥ የቆሻሻ ብዛቱ፥ የለማኙ አይነት፥ የሰውና የመኪና ግርግሩ" ትዝ ሲለኝ «ግን በምኑ ነው ከተማው አበባን የሚመስለው?» ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። ብጠይቅም መልሱን አላገኝም። ብቻ ዝም ብዬ «አወይ አዲስ አበባ!» እያልኩ እገረማለሁ።

ከረፋዱ አምስት ሰዓት አካባቢ ሆሳዕና ከተማ ገባን። እኔና ባለቤቴ ቁርስም ምሳም እንዲሆነን አንድ ምግብ ቤት ገባንና ጥብስ አዘዝን በላን። ከዚያም ወጣ ብለን ከመንገድ ዳር የጀበና ቡና አዘን ስንጠጣ ከመጣንበት አውቶቡሱ ውስጥ ሰዎች ስልክ ደውለው «እየወጣን ነው! ኑ!» አሉን። እኛም መኪናው የሚታየበት ቦታ ላይ ስለነበርን እውነትም ሲንቀሳቀስ አየነው። በፍጥነት ቡናችንን ጠጥተን በሩጫ ወደ መኪናው ሄደን ገባን። እኛ ብንገባም የተወሰኑ ሰዎች ገና አልመጡም ነበር። ረዳቶቹም «ሰው ይቀራል! እባክዎን ቀስ ይበሉ» ሲሉ ጨቅጫቃና ለሰዎች ክብር የሌለው ሾፌር ረዳቶቹን ሊሰማ አልፈለገም። እነዚህ የፈረደባቸው መንገደኞች ረጅም መንገድ ከመኪናው ኋላ ኋላ እየሮጡ ተከትለው እንደምንም አስቆሙት። መንገደኞቹም ገቡና ጉዟችንን ቀጠለን።

ወዳጄም ከምሳ ሲመለስ ቆሎ ገዝቶ ነበርና እንደተቀመጠ የቆሎ ግብዣ አቀረበልን። ባለቤቴ ለመብላት ባትፈልግም እኔና ወዳጄ እየበላን

ጨዋታችንን ቀጠልን። ወዳጄ ስለራሱ የሥራ ሁኔታ እያጫወተኝ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ደሞዛቸውን ብቻ መጠበቅ እንደሌለባቸው፣ በትርፍ ሰዓታቸው ተጠቅመው ተጨማሪ ሥራ በመሥራት ገንዘብ የሚያገኙበትን መንገድ እያነሳ ይመክረኝ ነበር። ጉዞው አድካሚ ስለነበር የተወሰነ ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ ወዳጄን እንቅልፍ ወሰደው።

እኔና ውድ ባለቤቴ የተለያዩ ወሬዎችን አልፎ አልፎም የግል ጉዳያችንን አንስተን እየተጫወተን ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት አዲስ አበባ ገባን። ወደ ዋናው መናኸርያ ሳንደርስ እኛ ቶታል ላይ ወረድን። በአዲስ አበባ የቆሻሻው፥ የሰውና የመኪናው ብዛት፥ የትራንስፖርቱ እጥረት፥ የድምጹ ብዛት ከበፊቱ ይልቅ በርክቷል። የምንሳፈርበትን ትራንስፖርት ለተወሰነ ደቂቃ ከጠበቅን በኋላ እንደ ምንም ከቶታል ወደ ዘነበወርቅ የሚሄድ ታክሲ አገኘን። ዘነበወርቅ ወርደን ወደምናርፍበት ቤት ሄደን። አወይ አዲስ አበባ! ዋናዋ መዲናችን!

ታምሩ ጥበቡ

# ተስፋ አልቆረጥንም

በከኮንሶና በአዲስ አበባ መካከል የአርባ ምንጭ ከተማ አለ። ስለዚህ ከኮንሶ ተነስቶ አዲስ አበባ ለመሄድ አርባ ምንጭ ማደሩ የግድ ነው። በእርግጥ ዛሬ አዲስ አበባ ስመጣ 4ኛ ጊዜዬ ነው። ከዚህ የተነሳ አዲስ አበባን በደንብ አውቀዋለሁ ብዬ አስባለሁ። በመሆኑም ወደ አዲስ አበባ የመሄድ ጉጉቴ እንደ ዱሮው አይደለም።

ይሁንና በእለተ ቅዳሜ ከጥዋቱ 12 ሰዓት ላይ ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ ብዬ እቃዬን ሁሉ በሻንጣ ከትቼ ነበር። ነገር ግን ብቻዬን ተነስቼ መሄድ አልችልም። ምክንያቱም ከእኔ ጋር አብሮኝ የሚሄደው ባልደርባዬ አዲስ አበባ ሄዶ ስለማያውቅ የግድ እሱን መጠበቅ አለብኝ።


ስለዚህ ባልደረባዬ እስኪመጣ ድረስ ፀጉሬን ለመስተካከል አሰብኩና ወደ ፀጉር ቤት ሄድኩ። ለካስ ቀኑ የእረፍት ቀን ነበርና ብዙ የመንግስት ሰራተኞች ፀጉራቸውን ለመስተካከል በጧቱ ወረፋ ይዘዋል። የወረፋው ብዛት ሴቶች በጧት የቧንቧ ውሃ ለመቅዳት የሚይዙትን ወረፋ ይመስላል። ይሁንና ተራዬን ጠብቄ ፀጉሬን ተስተካከልኩ። ከፀጉር ቤት እንደወጣሁ ባለደርባዬ ቢደርስም የመሄጃ ሰዓታችን ግን ገና አልደረሰም ነበር። ቢሆንም ሻንጣዬንና የጉዞ እቃዎቼን ለመውሰድ ወደ ትንሽዋ መኖሪያ ቤቴ ሄድኩ።

እኔና ባልደረባዬ ዋናውን የአስፋልት መንገድ ይዘን እየሄድን ሳለ ድንገት የባልደረባዬ መታወቂያ እቤት እንደተረሳ አወቅን። አሁንም

ቢሆን ሰዓቱ ገና ስለነበር ባልደረባዬ መታወቂያውን ለማምጣት በባጃጅ ወደ ቤቱ በረረ። እሱ እንደተመለሰ መንገዳችን ቀጠልን። እርምጃችንን እንደገና አስተካክለን የዋናውን መንገድ አስፋልት ይዘን ወደ አውቶቡስ ተራ ቀረብን። ለመሆኑ ስንት ሰዓት ነው ብዬ ሰዓቴን ለማየት የግራ እጄን ከፍ አድርጌ ሳይ ሰዓቴ እጄ ላይ የለችም። ለካስ ሰዓቴን ሳላስር ነው ከቤቴ የወጣሁት።

«ኸረ! ምን አይነት ቀን ነው!» አልኩ፤ በመገረም። ባልደረባዬም «ዛሬ መሄዳችን ይቅር እንዴ? ምንድ ነው ነገሩ?» ብሎ በድንጋጤና በሃዘን መንፈስ ጠየቀኝ። እኔም መልስ ሳልሰጠው ወዲያውኑ ሻንጣዬን ሰጠሁትና ሰዓቴን ለማምጣት ወደ ቤት በሩጫ ተፈተልኩ። ቤት እንደደረስኩ ጠረጴዛ ላይ በእቃ መካከል የተሸሸገችውን ሰዓቴን ሳብ አድርጌ ወሰድኳት። «ምነው? አዲስ አበባ ለመሄድ ፈርተሻል እንዴ?» አልኳት፤ ሰው ይመስል። በዚህ ጊዜ ሰዓቱ ወደ ስድስት ሰዓት ተቃርቧል።

እኔም በሩጫ አውቶቡስ ተራ ደረስኩ። ባልደርባዬ «መኪና አግኝቻለሁ! ምቹ ቦታም ይዣለሁ!» ብሎ በደስታ ተቀበለኝ። እኔም «የት ጋ?» አልኩ። እሱም «ሚኒባስ ውስጥ የኋለኛ ወንበር ላይ ነው» አለኝ።



«አዎን፥ ምቹ ቦታ ነው!» አልኩት ደስ ብሎኝ። መኪናው የሚንቀሳቀስበት ጊዜ ደረሰ። ጊዜው በጣም ስለሄደ መንገደኞች ከመሄዳቸው በፊት የሚበላና የሚጠጣ ማግኘት አለባቸው ብለን አሰብንና «ምሳ መብላት አለብን እኮ!» ብለን ጠየቅን። ረዳቱም «ኧረ እናንተ ምን ማለታችሁ ነው? ሰዓት አልፎአል እኮ!» አለን። እኔና ባልደረባዬም «ይሁን በቃ፤ አርባ ምንጭ ስንደርስ እንበላለን» አልን። ሰዓቱ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ሆኖል፤ ምንም ዓይነት ምሳ ሳናገኝ ወደ አርባ ምንጭ ተጓዝን። «ገና አዲስ አበባ ድረስ ልንጓዝ አይደል!» አልኩት ባልደረባዬን። ሚኒባሷ በዋናው የአስፋልት መንገድ ላይ እንደፈረሰ ትጋለባለች። አንዳንዴ ከብቶች ሲገቡባት ዳሩን ይዛ ታልፋለች። መንገደኞች እኛን ጨምሮ ደስ ብሏቸው እየተጫወቱ ነው።

በተለምዶ «ኮንሶ አሸዋ» ከሚባለው ቦታው ወይም ከካይሌ ወንዝ እስከ ሼሌ ማዞሪያ ባለው ጉዟችን ላይ አንድም ትራፊክ የለም። ባለ መኪናዎቹ ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ያገኙትን ተሳፋሪ ሲያወጡ ሲያወርዱ ዋሉ። ከካይሌ ወንዝ እስከ ጋቶ፥ ከጋቶ እስከ ጉማይዴ ማዞሪያ፥ ከጉማይዴ ማዞሪያ እስከ ኤልጎ ተሳፋሪዎችን ሲጭኑ ሲያወርዱ፥ እንደገና ሲጭኑ ሲያወርዱ እኛ በመሀል ተጉላላን።

«ኧረ እንሂድ» እያልን ወተወትን። ነገር ግን ብዙም አልተጨነቅንም። እንዲህ እንዲህ እያልንልክ ከቀኑ 10 ሰዓት ገደማ አርባ ምንጭ መናኸሪያ ገባን። ከፊጣኗ መኪናችን ወርደን ስንመለከት ከአዲስ አበባ፥ ከሃዋሳ፥ ከወላይታና ከጨንቻ የመጡ መኪናዎች እኛን ቀድመው ገብተዋል። መኪናዎቹ ወደ አዲስ አበባ እንድንሳፈርባቸው እኛን

የሚጠብቁ ይመስሉ ነበር። ደስታ በደስታ ሆንን። የመኪናዎቹ ቁመት፥ ርዝመት፥ ውበት በጣም አስገራሚ ነበር።

ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ አውቶቡስ ቲኬት መቁረጫ ቦታ ብዙ ወረፋ ነበር። ይባስ ብሎ «የአዲስ አበባ ቲኬት አልቋል» ተባልን። በዚህ መሃል ድንገት «የአዲስ አበባን መኪና ካጣችሁ ለምን ወደ ሃዋሳ አትሄዱም?» የሚል ሃሳብ ተወርወረልን። እኛም ጥሩ ሃሳብ ሳይሆን አይቀርም ማሰላሰል ጀመርን። ይሁንና ትንሽ አረፍ ብለን ስንመለከት ከእኛ በኋላ ለመጡ ሦስት ሰዎች የአዲስ አበባ ቲኬት ሲቆረጥላቸው አየን። በሁኔታው ብንናደድም ምንም ማድረግ ስለማንችል ዝም ብለን ወደ መኝታችን አመራን።

ሊመሽ አካባቢ ደግሞ አንድ አስገራሚ ነገር ሰማን። «ዘንድሮ ሰው ከእንቅልፉ ተነስቶ ወደ አውቶቡስ ተራ በማለዳ አይሄድም» አሉን። «ለምን?» አልን ሁለታችንም በመገረም እና በመደንገጥ። እነሱም በከተማው እየተወራው ስላለው ነገር እንዲህ በማለት አወሩልን፤ «አንድ ቀን አንድ ሰው ከጥዋቱ በ11 ሰዓት ከሴት ልጁ ጋር ወደ መናኸሪያ ሲሄድ ወንበዴዎች ያገኙታል። ወንበዴዎቹ በከተማ መካከል አባቷን ጨፍጭፈው ከገደሉ በኋላ ልጅቱን አቆሰሉ። ልጅቷ እዚሁ ሆስፒታል ታክማ ሕይወቷ ተረፈ። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ለሦስት ቀናት ተደገመ» የሚል አስደንጋጭ ወሬ ነገሩን። እኛም «እዚህ አካባቢ ህግ የለም እንዴ፤ ፖሊሶችስ የት ሄዱ?» ብለን ጠየቅን። ይሁንና ሁኔታውን ደጋግመው ሲነግሩን ነገሩ እውነት መሆኑን ተረዳን።

ያደርነው ከተማሪዎች ጋር ነበር። ከጥዋቱ 12 ሰዓት ላይ ተነስተን ግራ እና ቀኝ እየተመለከትን መናኸሪያ ደረሰን። ገና 12 ሰዓት ሙሉ ከፊታችን ስላለ መኪና አጥተን አዲስ አባባ ላንገባ እንችላለን ብለን ተስፋ አልቆረጥንም። የሚገርመው ነገር መናኸሪያ እንደገባን ሊሞላ ሁለት ወንበር ብቻ የሚቀረው የሀዋሳ መኪና ቆሟል። ከዚያም «የት ነው የምትሄዱት?» ብለው ጠየቁን። እኛም «አዲስ አበባ» አልን። ሁሉም ሰው ሳቅ በሳቅ ሆነ። ነገሩ ቢያስገርመንም «ወደ አዲስ አበባ መሄዳችን አይቀርም። ተስፋ አንቆርጥም።» ብለን ቲኬት ቆርጠን መኪና ውስጥ ገባን። መኪና ውስጥ እንግባ እንጂ ሃዋሳ የት እንደሆነ አናውቅም። መኪናውም መንቀሳቀስ ጀመረ። ሀዋሳም በሰላም ደረስን። ልክ 8 ሰዓት ሲሆን ደግሞ ከሃዋሳ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ መኪና አገኘንና ጉዟችንን ጀመርን። አዲስ አበባ ሁለት ሰዓት የማይሞላ መንገድ ሊሆን ይችላል ብለን አስበን ነበር። ነገር ግን እንዳሰብነው አልሆነም። መኪናው ይሄዳል፤ ይሄዳል መንገዱ ግን የሚያልቅ አይመስልም። ተስፋም ቆረጥን።

አዲስ አበባ መናኸሪያ እኛን ለመቀበል የሚጠብቁ ወንድሞች ነበሩ። አዲስ አበባ የምንደርስበት ሰዓት እየዘገየ ሲሄድ እነዚህ ወንድሞች ተስፋ መቁረጥ ጀመሩ። ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሳ እነዚህ ሰዎች ሳይጠፉ አይቀሩም እስከዚህ ሰዓት ድረስ ሊቆዩ አይችሉም ብለው ሲጨነቁ ነበር። የት አካባቢ እንደደረስን ለማወቅ ስልክ እየደወሉ ይጠይቁን ነበር። እኛም አገሩንና ከተማውን ስለማናውቅ ቀጫጭን ድንኳን የመሰሉ ቤቶች ጋር ስንደርስ በቃ አዲስ አበባ ገብተናል የሚል መልስ እንሰጥ ነበር። እነሱም እውነት እየመሰላቸው ሲጠብቁን ውለዋል። ይህ

ብቻ አይደለም የሚጠብቁን ወንድሞቻችን «አዲስ አበባ እንደገባችሁ ቃሊቲ መናኸሪያ ውረዱ፤ እዚያ እንጠብቃችኋለን» ሲሉን ምንም ስላልገባን ቃሊቲን አልፈን መርካቶ ገባን። ለካስ አዲስ አበባ ያሉት መናኸሪያዎች ሁለት መሆናቸውን ያወቅነው አሁን ነው። ይሁንና እድሜ ለዘመኑ ቴክኖሎጂ በስልክ ተፈላልገን ከምሽቱ 1፡30 መርካቶ መናኸሪያ ስንደርስ ወንድሞቻችን በሰላም ማግኘት ችለናል። ምስጋናችንን እያቀረብንላቸው አብረን ወደ መኝታ ስፍራችን አመራን።

ገብሬ ካራሳ ከጉተማ ኩሴ ጋር

## ከቱም እስከ አዲስ አበባ የ4 ቀን ጉዞ

ዕለቱ ሐሙስ ነበር። ጥዋት 1፡30 ከትንሹ ከተማችን ከቱም ተነስተን መኤኒት ሻሻን፥ መኤኒት ጎልዲያን አልፍን ስድስት ሰዓት ሙሉ ከተጓዝን በኋላ በ7፡30 ሸዋ ቤንች ደርሰን። ምሳችንን የምንበላበት ቦታ ደርሰን ልንወርድ ስንል አንድ ሽማግሌ ድንገት ተነሱ። ከዚያም በሰላም ስለመጣን እግዚአብሔርን ስለሁላችን ባርከው አመሰገኑ። ከዚያም «አሁን ምሳችሁን የምትበሉ ካላችሁ ብሉ፤ የፍየል ቅጠልም የምትይዙ ካላችሁ ያዙ» አሉ። እኛም ምን ለማለት እንደፈለጉ እያሰላሰልን ከመኪናችን ወረድን። ምሳችን በልተን ለግማሽ ሰዓት ያህል እረፍት ካደረግን በኋላ ወደ መኪናችን ገባን። መንገደኞች በሙሉ ተጠቃለው ከገቡ በኋላ ወደ ሚዛን ተፈሪ ከተማ ጉዟችንን ቀጠልን።

መንገዱ ጥሩ ስለነበረ መኪናው በፍጥነት እየበረረ ሳናስበው 9፡20 ሲሆን ዋጃ ማጂ ገባን። ከዋጃ ማጂ እስከ ሚዛን ተፈሪ ያለው ርቀት ሃያ ኪሎ ሜትር ገደማ ነው። የመንገድ ስራው ስላልተጠናቀቀ በዝናብ ወቅት ለመጓዝ በጣም አስቸጋሪ መንገድ ነው። ጋጀብ አካባቢ ስንደርስ በጣም እየዘነበ ነበር። መንገዱም ጭቃ በጭቃ ሆኗል። ከዚህ የተነሳ በርካታ መኪናዎች መንገድ ላይ ቆመዋል። የእኛም ሾፌር መኪናውን አቆመ። ከመንገደኞቹ ግማሽ ያህሉ ሁኔታውን ለማየት ወረዱ። ግማሾቻችን ደግሞ መኪና ውስጥ ተቀመጥን። ሾፌሩ ድንገት «በሩን ዝጉ!» ብሎ አዘዘ። በሩ ከተዘጋ በኋላ ሾፌሩ ማርሽ አስገብቶ በጎን

የቆሙትን መኪናዎች ቀስ እያለ አንድ በአንድ አልፎ እንደ ምንም ብሎ ብዙ ጭቃ ካለበት ቦታ ወጣ። ከእኛ በኋላ የቆሙት መኪናዎችም እኛን አይተው አንድ አንድ እያሉ መውጣት ጀመሩ።

ከእኛ መኪና የወረዱ መንገደኞም ፈጠን ፈጠን ብለው ጭቃውን አለፉና መኪናው ላይ ደርሰው ገቡ። «እፎይ!» ብለን ጉዟችንን ቀጠልን። ይሁንና ትንሽ ከተጓዝን በኋላ ሚዛን ልንደርስ በግምት ሁለት ደቂቃ ብቻ ሲቀርን መኪናችን በድንገት በጭቃ ተያዘ። ሾፌሩ እንደቅድሙ አሁንም አልፌ እሄዳለሁ ብሎ መኪናውን ከጭቃ ለማውጣት ታገለ። ሆኖም ጭቃው በጣም የሚያንሸራትት ስለነበር መኪናው ቀስ በቀስ ወደ ቀኝ እየተንሸራተተ አንድ ቦይ ውስጥ ገባ። በዚህ ጊዜ መኪናው ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ ክፉኛ ደንግጠው ጮኹ። መንገደኞችም ወርደው መኪናውን ከኋላ መግፋት ጀመሩ። መኪናውም ቀስ እያለ ወደ መንገዱ ገባና ጉዟችንን እንደገና ቀጠልን። በርግጥ ሾፌሩ በጭቃ ውስጥ የመንዳት ብዙ ልምድ እንዳለው ያስታወቃል። ብቻ እንደ ምንም ብለን ሚዛን ተፈሪ ገባን። መኪናችን በጭቃ ምክንያት መንገድ ላይ ብዙ ስላቆየን ጊዜው መሽቶ ነበር። ስለዚህ እኛ በደረስንበት ሰዓት ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ የሚሄደው የአገር አቋራጭ አውቶቡስ ቲኬት አይገኝም። በመሆኑም ማደሪያ ከመፈለግ ውጭ ልናደርግ የምንችለው ነገር አልነበረም። ስለዚህ ከመናኸሪያ ወጥተን አልጋ መፈለግ ጀመርን። አልጋውንም አግኝተን በሰላም አደርን። ምናልባት እስከ ጂማ እንኳ የሚያደርሰን መኪና ብናገኝ ብለን ጥዋት ተነስተን ወደ መናኸርያ ሄድን። መንገዱ በዝናብ ስለተበላሸም ይሁን አይታወቅም ምንም መኪና አላገኘንም።

ቀኑ አርብ ነው። ትንሽ አሰብን። አዲስ አበባ የሁለት ቀን መንገድ ነው። ፕሮግራማችንም ሰኞ ስለሚጀምር አዲስ አበባ እሁድ ከገባን ምንም ችግር አይኖረውም ብለን ወሰንንና ለቅዳሜ ቲኬት አስቆረጥን። ቀኑን ሚዛን ከተማ ውስጥ አሳለፍን። አመሻሽ ላይ የቅዳሜ ጉዟችንን እያሰብን በጊዜ ወደ ማደሪያችን ገብተን ተኛን።

ሌሊት ልክ 6፡30 ጓደኛዬ ተነስቶ ልብሱን ለባብሶ ሻንጣውን እያስተካከለ ሳለ ከእንቅልፌ ነቃሁ። እናም «አንተ! ምን ሆንክ?» ብዬ ጠየቅሁት። እሱም «11፡30 ተነስታችሁ ኑ ተብለን አልነበረም እንዴ? አሁን እኮ ይኸው 12 ሰዓት ሆኖአል!» አለኝ። እኔም ደንግጬ «እስቲ ሄድን ሰዓቱን እናርጋገጥ» አልኩት። ከዚያም ሌላዋ ጓደኛችን ወዳለችበት ክፍል በሩጫ ሄደን በሯን አንኳኳን። እሷም ደንግጣ ተነሳችና «ማን ነው?» ብላ ጠየቀች። እኛ መሆናችንን ካረጋገጠች በኋላ በሩን ከፍታ «ምን ነው? ችግር አለ?» ስትል ጠየቀችን። እኛም «ሰዓት! ሰዓት ስንት ነው? አለፈ እንዴ? ስንት ነው ሰዓቱ?» ብለን ጠየቅን። እሷ ሰዓትዋን አይታ «አይደለም! ረጋ በሉ እንጂ! ሰዓታችን በጣም ገና ነው። ገና 6፡30 እኮ ነው። ሂዱና ተኙ!» ብላ ነገረችን። እኛም ሳቃችንን ለቀቅን። እሷንም «ይቅርታ» ብለን ወደ ክፍላችን ተመልሰን ተኛን። ጥዋት እንደተባባልነው 11፡30 ተነስተን ወደ መናኸሪያ አመራን።


የአዲስ አበባው አውቶቡስ ትልቅ ነው። ጭቃ በመንገድ ላይ ቢኖርም ብዙ ሳንቸገር ከሚዛን ተፈሪ እስከ ቦንጋ ያለውን 100 ኪሎሜትር ተጓዝን። ቦንጋ 4፡40 ገባን። እዚያ እንደደረስን ሾፌሩ ለቁርስ ብሎ

አውቶቡሱን አቆመ። ሁላችንም ወርደን ቁርስ በላንና እንደገና ጉዟችንን ቀጠልን።

ከቦንጋ እስከ ጂማ ያለው ርቀት 100 ኪሎሜትር ገደማ ነው። መንገዱ ግን አስፋልት ስለሆነ ቶሎ ብለን ደረስን። ጂማ ስንደርስ ሰዓቱ ገና 6፡10 ነበር። እዚያም ትንሽ አረፍ ካልን በኋላ መኪናችን ነዳጁን ሞልቶ 7 ሰዓት ላይ እንደገና ጉዟችንን ቀጠልን። ረዥሙን መንገድ ያለ ምንም እረፍት ከተጓዝን በኋላ 11 ሰዓት አካባቢ ወልቂጤ ገባን። ሾፌሩም መኪናውን ሲያቆም ረዳቱ «ነገ ጥዋት ልክ 11 ሰዓት መኪናው ስለሚነሳ፥ አደራ! ሁላችሁም በጊዜ መጥታችሁ ተገኙ!» ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጠን። ማስታወቂያውን ሰምተን ሁላችንም ከመኪና ወረድን።

ወልቂጤ ማደሪያ አይጠፋምና በቀላሉ አልጋ አግኝተን ወደ ክፍላችን ገባን። ማታ ኃይለኛ ዝናብ ይዘንብ ስለነበር የትም ሳንሄድ አልጋ የያዝንበት ቤት እራታችንን በልተን ተኛን። ማለዳ በተባልንበት ሰዓት ሳንዘገይ ቶሎ ብለን ወደ መኪናችን አመራን። መንገደኞች ተሟልተው ከመጡ በኋላ ጉዟችንን ቀጠልን። መንገዱ አስፋልትና ሜዳማ ስለሆነ መኪናው በፍጥነት ይነጉዳል። ስለዚህ ብዙም ሳንቆይ ከጥዋቱ 3 ሰዓት አዲስ አበባ ገባን። ጉዟችንም በሰላም ተጠናቀቀ።

ወርቁ ኪያም እና አለማየሁ ቤንቲ





# ሞገደኛው ሾፌር

የመሰረተ ትምህርት አስተባባሪዎች ስልጠና በአዲስ አበባ ይሰጣል የሚል የረዥም ጊዜ እቅድ ነበር። እቅዱ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ ደረሰና እኔም ስልጠናውን ለመካፈል ግንቦት 10/2006 ዓ.ም. ከምኖርበት ጋሞ ጎፋ ዞን ከጨንቻ ወረዳ ከጦሎላ መንደር ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ተነሳሁ። ሻንጣዬን እንዲሁም አዲስ አበባ ለሚኖሩት ዘመዶቼ ያዘጋጀሁትን ቅቤና ፖም ይዤ ከማለዳው 11 ሰዓት ከሚሸኘኝ ከታላቁ ልጄ ጋር ወደ መናኸሪያ ግቢ አቀናሁ።

ከ30 ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ መናኸሪያ ግቢ ገባን። በመናኸሪያ ያለው የሰው ብዛት ልክ አልነበረውም። የትኛው ተጓዥ፣ የትኛው ሹፌ፣ የትኛው ደግሞ ሌባ እንደሆነ በውል አይታወቅም። በዚያ ሁሉ ግርግር ውስጥ ሰው ምን ውስጥ እንደሚገባ አይታወቅም። ብቻ ትርምሱ ብዙ ነው።

እንደ ምንም ብዬ ቀደም ሲል የቆረጥኩት ቲኬት ላይ ያለውን የመኪናዬን ጎን ቁጥር አየሁና፥ መኪናዬን ፈልጌ ገባሁ። መኪናው ትልቁ የአገር አቋረጭ ሲሆን ደረጃ አንደኛ ነው። እድለኛ ሆንኩና የአገኘሁትም የወንበር ቁጥር 1ኛ ሆነ። «አቤት እድሌ!» አልኩ በወንበሬ ላይ ተቀምጬ። «እግዚአብሔር ሆይ! ተመስገን!» ብዬ ምስጋናዬን ለፈጣሪዬ አቀረብኩ። መኪናዬንም ቦታዬንም በሰላም ስለአገኘሁ ከመጠን በላይ ደስ ብሎኛል። ሻንጣዬን ተሸክሞ የሸኘኘኝን ልጄን «በል ሂድ፥ እኔ ተሳፍሬያለሁ፥ በሰላም ቆዩልኝ» ብዬ ወደ ቤት እንዲሄድ አሰናበትኩት።

ከማለዳው 12፡30 ሲሆን ከጨንቻ መናኸሪያ ወደ አዲስ አበባ ጉዟችንን ጀመርን። ተራራዎቹ ላይ የነበረው ቀዝቃዛ የአየር ፀባይ ወደ ታች እየወረድን፥ እየወረድን ስንሄድ ቅዝቃዜው ቀስ በቀስ እየቀነሰ እየቀነሰ ሄዶ አባያ ሃይቅ ስንደርስ ወደ ከፍተኛ ሙቀት ተቀየረ።

በመኪናው ውስጥ የሚሰማው የሙዚቃ ጩኸት ገና ከመናኸሪያ በር ስንወጣ ነበር የጀመረው። የሙዚቃው ጩኸት የተለያዩ ሙዚቀኞችን እያፈራረቀና የአእምሮአችንን ሰላም እየተሻማ ልክ ከቀኑ 5፡30 ላይ ሆሳዕና ደረስን። ሆሳዕና ምሳ ለመብላት ወረድን። ከ30 ደቂቃ የምሳ እረፍት በኋላ የአዲስ አበባ ጉዟችንን ቀጠልን።

ጉዟችንን አጋምሰናል፤ ሙቀቱም ጨምሯል፤ ድካሙም በርትቷል። አብዛኛው ተጓዥ በእንቅልፍ ተሸንፏል። በዚያ መካከል ያልታሰበ አንድ ክስተት ተፈጠረ። ከመካከላችን አንድ ሱሪ የታጠቀች እህት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ወደ ሾፌሩ ሩጫዋን ቀጠለች። «እባክህን መኪናውን አቁምልኝ!» አለች።

«ምነው? ምን ሆንሽ?» ሲል ጠየቃት ሾፌሩ። እሷም «እባክህ ሽንቴ ወጥሮኛል!» አለች፤ ፊቷ ላይ ጭንቀት እየታየ። «አይቻልም!» ብሎ ሾፌሩ መንዳቱን ቀጠለ። ልጅቷ ግን በጣም እንደተጨነቀች ግልጽ ነበር። በመጨረሻም ጭንቀቷን አይቶ አቆመ። ሾፌሩ ሞገደኛ ኖሯል ለካ መኪናውን ያቆመው ምንምን ዓይነት ጫካ በሌለበት አውላላ ሜዳ ላይ ነበር። ይኸው ሞገደኛ መኪናውን አቁሞ «በይ፥ ውረጂ! ቶሎ ሽንትሽ ተመለሺ!» አላት።

ይህች ሴት በጣም ተጨንቃ ስለነበር የምትጠጋበትን ጫካ ፍለጋ ወደ ግራ ወደ ቀኝ፣ ወደ ላይ ወደ ታች እያለች ሩጫዋን ቀጠለች። ላይ ታች ብትልም እርቃኗን የሚሸፍን ነገር ስታጣ ዓይኗን ጨፍና ወደ መንገዱ ዞር አለችና ቢያንስ ከአንድ ሰዓት በላይ ያስጨነቃትን ፈሳሽ ለማስወጣት ተገደደች።

በሁኔታዋ የተገረመውና የተናደደው ሞገደኛው ሾፌር «እባክሽ ተነስተሽ ግቢ! እብድ ነሽ እንዴ?» እያለ አመናጨቃት። ከኋላዋ ተቀምጠው ሁኔታዋን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ይከታተሉ የነበሩ ታዛቢዎች እንዲህ ሲሉ ጠየቋት «በእውነት አንችን ያሳበደው ወይም ያሰከረው ከጥግሽ የተቀመጠው የጓደኛሽ ፍቅር ነው፥ ወይስ ሆሳዕና ከምግብ በኋላ የጠጣሽው ድራፍት ነው?» ሲሉ በሹፈት ጠየቋት። እሷ ግን ጆሮ ዳባ ብላ ዝምታን መረጠች።

ያ ብቻ አይደለም፤ ከሌሎችም የሚወረወርባትን ቃላት ሁሉ እየሰማች እንዳልሰማ ሰው ማለፍን ብቸኛ አማራጭ አደረገች። ከጓደኛዋ ጋር እየተላፋች ጉዞዋን ወደ ፊት ቀጠለች። እኔም አንዴ ስገረም፣ አንዴ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ እያልኩ ስመራመር ሰዓቱ ነጎደ።

በመጨረሻም የብርዱን ክብደት አልፈን፣ የሙቀቱን ሃይል ችለን፣ የልጅቱን አሳፋሪና አይን አወጣነት እያየን በአስር ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ገባን።

ደስታ ብርሃኑ



# ሰው ቃሉን አይመስልም

ቀኑ ቅዳሜ ግንቦት 7 /2006ዓ.ም. ሲሆን እኔና ጓደኛዬ ከሚዛን ተፈሪ ወደ አዲስ አበባ ለመጓዝ የጎን ቁጥሩ 6226 በሆነ አውቶቡስ ውስጥ ገብተናል። ከተጓዦች መካከል አንድ በአርባ ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሼህ ሁሴን የሚባሉ በጣም ተጫዋች፣ ደግና ጥሩ ምክር መካሪ ሰው ነበሩ። በጉዟችን ወቅት በጨዋታ እያዋዙ ወጣቶችን ይመክሩ ነበር። «ወጣቶች እንደ እኔ ለመምከርና ለመከበር ራሳችሁን ጠብቁ፤ በእድሜአችሁ መልካም እየሰራችሁ እደጉ፤ አትባልጉ» ይሉ ነበር። ባለትዳሮችንም «እናንተ ባለትዳሮች ለሴቶቻችሁ ጨዋ ሁኑ» እያሉ ቀልድ አዘል ቁም ነገር ያስጨብጡን ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ፊቱንና መላ አካላቱን በጋቢ የሸፈነና በፀጥታ የተቀመጠ አንድ ሰው በአውቶቡስ ውስጥ ነበር። ሼሁ ዞር ብለው «ምን ነው ወንድሜ? በዚህ ሁሉ ሰው መሃል ብቻህን ሆንክ? ተው! ምን አባቱ ሁሉን እርሳው፣ ዛሬን ሳቅ» አሉት። ያም ሰው ፊቱን ገለጥ አድርጎ «ተውኝ! እኔ አንድ እግሬን አጥቼ በሃዘን ላይ ያለሁ ሰው ነኝ። እስቲ ሳቁን ትቼው በዝምታ ነፍሴን ላጽናናት። አትምጡብኝ፤ ብቻዬን ተውኝ!» አለ በቁጣ። ሼሁም መልሰው «እውነትህን ነው! ወንድ ልጅ እንደዚህ ነው፤ በዝምታና በፀጥታ ጭጭ ብሎ ነው ለራሱ የሚናገረው፤ 'ኡኡ! ስሙኝ' አይልም፤ አይዞህ! ዝምታህን ስታበቃ ግን ተቀላቀለን» አሉት።

ድንገት ከፊት ለፊት «ኧረ! ኧረ!» እያሉ ጮኹ። ለካስ አንዱ ድንገት ሆዱ ውስጥ የገባውን ሁሉ ምንም ሳይቆጥብ ፊት ለፊቱ በተቀመጠው ሰው ጫንቃ ላይ ደፍቶበት ኖሯል። ሼሁም ወደላይ ያለው ሰው እንዳይጨነቅ በአካባቢው ያሉትን ሰዎች «ለምን ትቆጡታላችሁ? እስቲ ማን ወዶ እንደዚህ መሆን ይፈልጋል? እሱን ተውትና ለራሳችሁ እንዲህ ያለ ነገር አይግጠመኝ በሉ እንጂ» ብለው በተለመደው ቀልድ መሰል ለዛቸው ቁም ነገራቸውን ጣል አደረጉ።

እንደዚህ ባለ ሳቅና ጨዋታ ቦንጋ ደርሰን ለቁርስ ወረድን። ተመልሰን ጉዞ ስንጀምር ሼሁ ቆመው «አዳምጡኝ! አላህ፥ በሆዳችን የገባውን ያቆይልን!» ሲሉ ሁሉም «አሜን!» አለ። ሼሁ ከተቀመጡ በኋላ ያ አንድ እግሬን አጥቻለሁ ብሎ በሃዘን የነበረው ሰው ወደ ሼሁ ዞር አለና «ሼሂ! ምን አጥፍቼ ነው አንድ እግሬን ያጣሁት? እባክዎ አላህን 'እግሩን መልስለት' ብለው ፀልዩልኝ?» አለ። ተሳፋሪው ሁሉ አንድላይ ሳቀ። ሼሁም መልሰው እንዲህ አሉት «ምን ያደርግልሃል? አይጠቅምህም ብሎ እኮ ነው የወሰደው» በዚህ ጊዜ እሱም አብሮ ሳቁን ለቀቀው።

ጂማ መግቢያ አካባቢ ስንደርስ አንዷ ከመቀመጫዋ ተነስታ «እባካችሁ ፌስታል! ፌስታል!» እያለች ጮኸች። ለካስ አንዷም በተራዋ ዝቅ ብላ በአውቶቡስ ወለል ላይ እያዘነበችው ነበር።

ቀስ በቀስ ግን ያ ሁሉ ድምፅ እየቀነሰ ፀጥታ እየሰፈነ መምጣት ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ ፀጥታና የአንገት መወዛወዝ ብቻ አውቶቡሱን ገዛው። ጊቤ ለፍተሻ ስንወርድ ሰው ሁሉ የተለመደውን ሞቅ ሞቅ የሚያደርግ

ነገር ለመፈግ መሯሯጥ ጀመረ። እኔና ጓደኛዬም ሻይ ቡና ብለን ተመልሰን ወደ መኪናችን ገብተን ቁጭ አልን። እንደገና ጉዞው ተጀመረ። በፀሃዩ ሙቀት ላይ የሰው ጩኸትና በአውቶቡሱ የሚሰማው ሙዚቃ ተደማምሮ መኪናውን መጓጓዣ ሳይሆን ጭፈራ ቤት አስመስሎታል።

ቀኑ ለዐይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ወልቂጤ ገብተን ሁላችንም ለአዳር ተበታተንን። እኔና ጓደኛዬ የአርሴናልንና የሀልሲቲን ጨዋታ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን (ETV) ለማየት ታድመን ነበር። ከጨዋታው በኋላም በአርሴናል ውጤት ተደስተን ወደ ማደሪያችን ገባን።

በማግስቱ በቀጠሯችን መሰረት ጉዞ ለመጀመር ከሌሊቱ 10፡30 ከማደሪያችን ስንወጣ ዓይኔን ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ አንድ ነገር ተመለከትሁ። የሆነ መብረቅ ከላይ የወደቀ እስኪመስለኝ ድንጋጤና ግራ መጋባት አፈዘዙኝ። ሼሁ ናቸው። አብራን ስትጓዝ ከነበረች ቢበዛ 19 ዓመት ከምትሆን ወጣት ጋር ከአንድ ክፍል እየወጡ አየኋቸው። ወጣቷ የጠይም ቆንጆ ስትሆን በጉዟችን ወቅት ከአጠገባቸው በፀጥታ ተቀምጣ ትጓዝ ነበር።

«ከዚህ በኋላ በዚያ አውቶቡስ እንዴት ብዬ ነው የምጓዘው? ከዚህስ በኋላ ሼኩ ቢናገሩ እንዴት አምኜ ልሰማቸው እችላለሁ? አቤት እንዲህ አይነት ሰውም አለ ለካ» ብዬ ገና ንግግሬን ሳልጨርስ ጓደኛዬ ከአፌ ቀበል አደረገና «ና እንሂድ እባክህን! ሰው ቃሉን አይመስልም» አለኝ። በቃ! ተቆጣሁ። ቁጣዬን ግን ለራሴ አስቀረሁት።

የማለዳው ጉዞ የተጀመረው ሌሊት በመሆኑ ፀጥ ባለ ሁኔታ ተጉዘን ልክ 2፡30 አዲስ አበባ ገባን። ገና አውቶቡሱ እንደቆመ ሼሁ በፍጥነት ወጡና ዞር ብለው ሳያዩ አቀርቅረው ሄዱ። ያች ወጣትም ከመኪናው ስትወርድ ልክ እንደ እርሷ ወጣት የሆነ ልጅ «Honey!» ብሎ ሲያቅፋት እሷም ተጠመጠመችበት።

እኔም ብጮህ ኡኡ ብል ደስ ባለኝ ነበር። ግን ማን ደፍሮ እውነቱን ለተበዳይ ሊነግረው ይችላል? እኔም በዝምታ ያየሁትን አይቼ ያንን ወጣት «ተው ራስህን ጠብቅ» ሳልለው ትቼው ሄድኩ። እኔም ሼሁም ጥፋተኞች ነን። ይቅር! ሁሉም ይቅር! ሰው እንደሆን ያው ሰው ነውና።

እንዳሻው ተሾመ ከጌርጌሬ ሲራሉት ጋር

# ከደራሼ እስከ አዲስ አበባ

እኔ አለምነሽ ኩሲያ እባላለሁ። አቶ ዮናስ ኃይሌ ደግሞ በጉዞ አብሮኝ የነበረ ነው። እኔና አቶ ዮናስ ኃይሌ የምንኖረው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል ሰገን ዞን ደራሼ ወረዳ ውስጥ ነው። ግንቦት 8/2006 ዓ.ም ካለንበት አካባቢ ተነስተን በመኪና አርባ ምንጭ ከተማ ገባን።

በዚያው ቀን ወደ ማታ አካባቢ አርባ ምንጭ መናኸሪያ ሄጄ ወደ አዲስ አበባ መሄድ የሚያስችለንን የአገር አቋረጭ አውቶቡስ ቲኬት ለሁለታችንም አስቆረጥኩ። ከዚያም እራት በልተን ሁለታችንም በየማደሪያ ቦታችን ገብተን በሰላም አደርን።

በነጋታው ማለዳ 11 ሰዓት ሲሆን ከእንቅልፋችን ነቅተን ስልክ ተደዋወልን ተገናኘንና ወደ መናኸሪያ አመራን። እዚያ እንደደረስን አዲስ አበባ ወደሚሄደው አውቶቡስ ውስጥ ገባን። የቆረጥነው ቲኬት ላይ በሰፈረው የመቀመጫ ቁጥር መሰረት ወደ መቀመጫችን ስንሄድ ቦታው ባልጠበቅናቸው ሌላ ተጓዦች ተይዞ አገኘን። እኛም በፀባይ ቀርበን «ይቅርታ፥ ይህ ቦታ እኮ የእኛ ነው። እናንተም በቲኬት ቁጥራችሁ መሰረት ወንበራችሁን ፈልጋችሁ ብትቀመጡ አይሻልም?» በማለት በትህትና ጠየቅናቸው። ለካስ እነሱ ትዕቢተኞች ነበሩ። ቦታችንን መልቀቅ ይቅርና በመልካም ፀባይ እንኳ ለጥያቄያችን ምላሽ አልሰጡንም። ይልቁንም በኃይለ ቃልና በትዕቢት «እናንተንም ሆነ የቲኬቱን የወንበር ቁጥር አናውቅም። ከፈለጋችሁ ወደ መጨረሻ አካባቢ

ወንበር ፈልጋችሁ ተቀመጡ እንጂ ቦታውን አንለቅላችሁም!» ብለው ቦታችንን ከለከሉን።

እኛም በሰዎቹ ሁናቴ ብናዝንም «ይሁን በቃ» ብለን ወደ መሃል አካባቢ ቦታ ፈልገን ተቀመጥን። ከዚያም ከጠዋቱ 12 ሰዓት ሲሆን ሾፌሩ የአውቶቡሱን ሞተር አንቀሳቀሰ። የመናኸሪያውም መውጫ በር ተከፍቶ፥ ጉዟችንን ጀመርን።

ከአርባ ምንጭ ተነስተን የተወሰነ ርቀት ከተጓዘን በኋላ ሁለት ሰዓት አካባቢ ጫኖ መንደር ደረስን። በጫኖ መንገድ ዳር ማንጎ የሚሸጡ ልጆች አሉ። መኪናውም ለትንሽ ጊዜ ቆመ። እኛም በመስኮት ብቅ ብለን ማንጎ ገዛን። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ጉዟችንን ቀጠለን። የቁርስ ሰዓት ሲደርስ ከገዛነው ማንጎ ላይ አንድ አንድ ወስደን በላን። የጫኖ ማንጎ በጣም ይጣፍጣል!



መኪናው ጉዞውን ቀጥሏል። ልክ ሶስት ሰዓት ሲሆን ወላይታ መናኸሪያ ደረስን። እዚያም ሾፌሩ መኪናውን አቁሞ ለተወሰነ ጊዜ አቆየን። ከአጭር ቆይታ በኋላ እንደገና ተነስተን ከወላይታ ወደ ከምባታ ዞን የሚወስደውን ተራራማውን መንገድ ተያያዝነው። ስድስት ሰዓት ሲሆን ሆሳዕና ከተማ ገባን። ሆሳዕና እንደደረስን ምሳ እንድናደርግ ሾፌሩ መኪናውን አቆመልን። እኛም እንደሌሎቹ ተሳፋሪዎች ከመኪናው ወርደን በየአይነቱ የሚባለውን ምግብ አዝዘን በላን፤ ውሃም ጠጣን። ምሳችንን ከጨረስን በኋላ እጃችን ታጠብን ቀጣዩን ጉዞ

መጠበቅ ጀመርን። የጉዞው ሰዓት ሲደረስ እንደገና መኪናው ውስጥ ገብተን ቦታችንን ያዝን። መኪናው ተንቀሳቅሶ ከፊታችን ያለውን መንገድ ተያያዘው። ከበላነው ጥሩ ምሳ ይሁን፣ ከመንገዱ ርቀት አይታወቅም ሰውነታችን በጣም ደክሟል። ዓይኖቻችንም ከብደው እንቅልፍ እንቅልፍ ስላለን ተኛን።

ብቻ ሁሉን ተቋቁመን ወደ አስር ሰዐት አካባቢ እዚሁ አዲስ አበባ በሰላም ገባን። በመጨረሻም ጉዟችንን በሰላም ስላጠናቀቅንና ያለ ምንም ችግር አዲስ አበባ ስለገባን እግዚአብሄርን እጅግ አድርገን አመሰገንን።

አለምነሽ ኩሲያ ከዮናስ ኃይሌ ጋር



## መብት ረጋጩ ሾፌር

ግንቦት 2006 ዓ/ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ነበር ከአንደራቻ ወረዳ ከዱዓና ቀበሌ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት የተነሳሁት። እኔ ካለሁበት የገጠር ወረዳ ተነስቶ አዲስ አበባ ለመግባት በርካታ የገጠር ከተማዎችን ማለፍ የግድ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከአንዱ ከተማ ወደሌላው ከተማ ለመሸጋገር የትራንስፖርት ችግር የሚያጋጥምበት ጊዜ አለ። እኔም ወጌጫ ከምትባል ከአንድ የወረዳ ከተማ ተነስቼ ቴፒ ለመድረስ 4 ሰዓት ሙሉ የትራንስፖርት መኪና ጠብቄያለሁ። ከዚያም ከቀኑ 8 ሰዓት አካባቢ አንድ መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ መኪና አገኘሁና አመሻሽ ላይ ወደ 11፡30 አካባቢ ቴፒ ከተማ በሰላም ገባሁ።

ልክ ከተሳፈርኩበት መኪና ስወርድ ከኔ ጋር አብሮ ወደ አዲስ አበባ ከሚመጣው ጓደኛዬ ጋር ተገናኘንና ሰላም ተባባልን። ሁለታችንም በጣም ስለራበን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ «ምሳ በልተሃል?» «ምሳ በልትሃል?» ተባባልን። ጓደኛዬ «አንተን ስጠብቅ መቼ በላሁ!» አለኝ። ለካስ ይኸው ጓደኛዬ እዚያው ቴፒ ከተማ ላይ እኔኑ ሲጠብቅ ቀኑን ሙሉ ምሳ ሳይቀምስ ጦሙን ውሏል። እኔም «አንተን ሳላገኝ አልበላም ብዬ መቼ በላሁ!» አልኩትና ተያይዘን ምግብ ወደሚገኝበት ሆቴል አመራን። ወደ 12 ሰዓት አካባቢ አንድ ሆቴል ገባንና በያይነቱ የሚባለውን የምግብ ዓይነት አዝዘን መክሰሳችንን በላን።

ረሃባችንን ካስታገስን በኋላ ቀጣዩ ተግባራችን ኮተታችንን የምናሳርፍበት አልቤርጎ ማግኘትና ሻንጣችንን አስቀምጠን ወደ አዲስ አበባ የምንሳፈርበትን ቲኬት መፈለግ ነበር። በዚሁ መሰረት ግዮን ወደሚባል ሆቴል አመራንና አልጋ ጠየቅን። እንዳጋጣሚ የቤርጎ ቁጥር አራት ክፍት ሆኖ አገኘንና እሱን ተከራይተን ሻንጣዎቻችንን አስቀመጥን። ትንሽ አረፍ ካልን በኋላ በራችንን ዘግተን ወደ አዲስ አበባ የምንመጣበትን የአውቶቡስ ቲኬት ፍለጋ ወጣን። ብዙም ሳንደክም የጉዞ ቲኬት አገኘንና 420 ብራችንን ከፍለን ቆረጥን።

አሁን በመጠኑም ቢሆን ውጥናችን የተሳካ ይመስላል። ስለዚህ ትኩስ ነገር ፈልገን እየጠጣን ለመጫዋወት አመቺ ነው ብለን ወዳሰብነው ቴፒ እና ፍሬዎቿ ካፌ ገባን። እዚያም ቁጭ ብለን ስንጫዋወት ካንዱ የሆቴል ተጠቃሚ ጋር በጨዋታ ተገናኘንና ወዳጆች ሆንን። ከእሱ ጋር የተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮችን እያነሳን ስንጨዋወት አመሸን። ከዚያም እዚያው ያፈራነው ወዳጃችን ሶስታችንም የጠጣነውን የማኪያቶ ሂሳብ ከፍሎ ለመሄድ ተነሳ። እኛም አመስግነን እሱን ከሸኘን በኋላ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ማህበራዊ የሚባል የምግብ አይነት ወደሚሸጥበት ሆቴል ገብተን ሁለት ምግብ አዝዘን እራታችንን በላን።

ከዚያም ወደ ማደሪያ ቦታችን ተመልሰን የተከራየናት ቤርጎ ውስጥ ገባን። ቤርጎ ከገባን በኋላ ብዙ ጊዜ ሳናጣፋ ከተጣጠብን በኋላ ልብሳችንን ቀያይረን ወዲያው ተኛን። ያሳለፍነው ሌሊት ሰላማዊ ነበር። ያለ ምንም ችግር ጥሩ እንቅልፍ አሳልፈን ከንጋቱ 11፡30 ሲሆን ከእንቅልፋችን ነቃን። ልብሳችንን ለባብሰን ፊታችንን ከተጣጠብን በኋላ

ማታ ያስያዝነውን መታወቂያችንን የጥበቃ ሰራተኛው እንዲመልስልን ቀሰቀስነው። የጥበቃ ሰራተኛውም መታወቂያችንን መልሶ እኛን ለማሰናበት አስቀድሞ የተኛንበትን ክፍል ፈትሾ ማረጋገጥ ስላለበት ቤርጎውን ከፈታተሸ በኋላ መታወቂያችንን ሰጥቶ የቤርጎውን የውጭ በር ከፍቶ አሰናበተን። ፈጠን ፈጠን ብለን ወደ መናኸሪያ አመራንና የምንጓዝበትን አውቶቡስ አግኝተን ትኬታችን ላይ በተመለከተው የወንበር ቁጥር መሰረት ወንበራችን ላይ ተቀመጥን።

አንድ በእድሜያቸው ሸምገል ያሉ አዛውንት ትኬታቸው ላይ ያለውን የወንበር ቁጥር ባለማወቅ ይሁን ወይም የወንበር ቁጥሩ ትኬቱ ላይ ባለመጻፉ ያገኙት ወንበር ላይ ቁጭ አሉ። የወንበሩ ባለቤትም መጥቶ «አባባ ተነሱ! ይህ የእኔ ወንበር ነው» አላቸው። እሳቸውም «እሺ» ብለው ተነሱና አጠገቡ ካለው ሌላ ወንበር ላይ ቁጭ አሉ። አሁንም እንደቀድሞው ወንበሩ ላይ መቀመጥ የሚገባው ሌላ ተሳፋሪ መጣና «ተነሱ አባባ! ይሄ የእኔ መቀመጫ ነው» አላቸው። እሳቸው አሁንም «እሺ» ብለው ተነሱና ሌላ ወንበር ላይ ተቀመጡ። እንዲህ እንዲህ እያሉ በርካታ መቀመጫዎችን አዳረሱ።

ታዲያ በሁኔታው ያዘኑ ተሳፋሪዎች ትኬታቸውን ተቀብለው ሲመለከቱ ትኬቱ ላይ የወንበር ቁጥር እንዳልተጻፈበት አረጋገጡ። ይህን ስህተት የፈጠረው ረዳቱ ለሚፈልጋቸው ሰዎች ጥሩ መቀመጫ ለማስቀረት ሆን ብሎ ያደረገው ስህተት መሆኑን አውቀው ረዳቱን አንቀው ያዙት። ከዚያም «አንተ፥ ሌባ! ኪራይ ሰብሳቢ! ይህን ያደረግኸው ሆን ብለህ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ሲመጡ ለእነሱ ወንበር ለመስጠት አስበህ እንደሆን


አውቀናል!» በማለት ከዚህም ከዚያም አዋክበው መልስ አሳጡት። ከዚያም «በል እኝህን አባት ጥሩ ወንበር ፈልገህ ካላስቀመጥክ ጉድህ ነው!» ብለው ከዛቱ በኋላ ለቀቁት። ረዳቱም ስህተቱን ራሱ ሆን ብሎ የፈጸመው መሆኑን አውቆ ምቹ ወንበር ፈለገና አስቀመጣቸው። ከዚህ አስገራሚ ትእይንት በኋላ ጉዟችንን በሰላም ቀጠልን።

የተሳፈርንበት አውቶቡሱ ፈጣን ነው። የጧቱ ቅዝቃዜ ለረፋዱ ሙቀት እየለቀቀ ነው። እኛም ማለዳ በወንበር ምክንያት የተፈጠረውን ውዝግብ እንስተን እየተጫዋወትን ከረፋዱ 4 ሰዓት ቦንጋ ከተማ ደረስን። ሾፌሩ አውቶቡሱን አቆመ፤ ረዳቱም «ለቁርስ 20 ደቂቃ ብቻ» የሚል ማስታወቂያ ተነግሮን በሩን ከፈተልን። እኛም «ቢትዋ» የሚባል ሆቴል ገብተን ቁርሳችንን ከበላንና ትኩስ ነገር ከጠጣጣን በኋላ ተመልሰን ወደ አውቶቡሳችን ገብተን ወንበራችን ላይ ተቀመጥን። ፈጣኑ አውቶቡስ በተመቻቸው አስፓልት ላይ እየበረረ ከቀኑ 8 ሰዓት ጂማ መናኸሪያ አስገባን።

እኛም ማደሪያችን ጂማ መስሎን «እሳይ! በሰላም ወደ ማደሪያ ቦታችን ያደረስከን ፈጣሪ ተመስገን!» እያልን ሻንጣችንን ካስቀመጥንብት ቦታ ወጣ ወጣ ስናደርግ፣ ሾፌሩና ረዳቱ በጩኸት «እንዴ! ምን እያደረጋችሁ ነው? እዚህ የምትወርዱት ጂማ የምትቀሩ ብቻ ናችሁ፤ አዲስ አበባዎች ጉዞ እንቀጥላለን፤ የምናድረው ወልቂጤ ነው!» ሲሉ ያልጠበቅነውን ነገር ነገሩን።

ተሳፋሪዎችም እርስ በርሳቸው «ምንድነው ነገሩ! ምን ጉድ ይሄ! እንዴት ሊሆን ይችላል?» ተባባሉ። ይሁን እንጂ ሾፌሩም ሆነ ረዳቱ

መሄዳችን የግድ ነው ብለው ወስነዋል። ረዳቱም የአውቶብሱን በር ዘጋ፤ ሾፌሩም የአውቶቡሱን ሞተር ሞቅ ሞቅ ሲያደርግ ጉዞው እርግጠኛ መሆኑን ስላረጋገጥን ማጉረምረማችን አቁመን ጉዟችንን ቀጠልን። ሾፌሩ ፍጥነቱን ጨምሯል። ከዚህ የተነሳ አውቶብሱ ሞተር ሳይክል እንጂ አውቶብስ አይመስልም ነበር። በዚህ ፍጥነት ላይ አንድ ነገር ቢያጋጥመው አውቶብሱ ሊገለበጥ ይችላል በሚል ስጋታችን ጨምሯል፤ መንፈሳችንም በፍርሃት ተውጧል።



የመኪናውን ፍጥነት በተመለከተ በአውቶብሱ ውስጥ ያሉት መንገደኞች በሁለት ሃሳብ መከፈል ጀምረዋል። አንደኛው ቡድን ሾፌሩ የአውቶብሱን ፍጥነት ጨምሮ እንዲነዳና ቶሎ እንዲደርስ የሚፈልግ ነው። ሌላው ቡድን ደግሞ እንደዚህ ከሚበር ፍጥነቱን ቀንሶ በገባበት ሰአት ቢገባ ይሻለናል የሚል ነው። በመጨረሻም ፍጥነቱን ይጨምርና ቶሎ ይግባ የሚለው ቡድን በረታና በፊትም መብረር የፈለገው ሾፌር ድጋፍ አግኝቶ ለምሳ እንኳን ሳያሳርፈን እየበረረ ሄዶ ጊቤ ድልድይ ላይ አደረሰን።

ምሳ ሳያገኙ በጉዞ የደከሙት ተሳፋሪዎች ጊቤ ድልልድይ ላይ እንደደረሱ «አወርደን! ቶሎ እንመለሳለን፤ አውረድን!» ብለው ከወረዱ በኋላ የገብስ ቆሎና የጀበና ቡና ገዝተው መቀማመስ ጀመሩ። የሰው መብት የማያውቀው ሾፌር እንደልማዱ «ቶሎ ግቡ!» እያለ የአውቶቡሱን ሞተር «ሞቅ ሞቅ» ከላከሱንም «ጲጵ! ጲጵ!» እያደረገ ተሳፋሪዎቹን ግራ ማጋባት ጀመረ። ተሳፋሪዎቹም «ኧረ! ጥሎን እንዳይሄድ!» እያሉ የገዙትን ቡና ሳይጠጡ ቆሏቸውን ብቻ ይዘው እየሮጡ ወደ አውቶቡሱ ገቡ። ሾፌሩ እንዲሁ እንደተጣደፈ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወልቂጤ ይዞን ገባ።

ወልቂጤ እንደደረስን የቀኑን ጉዟችንን ያጠናቀቅን መስሎን «እሰይ! ወደ ማረፊያ ቦታችን በሰላም ደረስን!» እያልን ለመውረድ መዘጋጀት ጀመርን። ረዳቱም ከተቀመጠበት ተነስቶ በመንገደኞች መሃል እየተንጎራደደ «ወልቂጤ ወራጆች? ወልቂጤ ወራጆች?» እያለ መጠየቅ ጀመረ። እኛም የጉዞ ቲኬት የሚሰበሰብ መስሎን ዝም አልን። የወልቂጤ ወራጆች ከወረዱ በኋላ እኛም እዚያው የሚያሳድረን መስሎን ሻንጣችን ከሰቀልንበት ማውረድ ጀመርን። ይሁንና ሾፌሩም ሆነ ረዳቱ «አዲስ አበባ ገብተን ማደር አለብን፤ እዚህ በፍጹም ማደር የለብንም!» ብለው አቋማቸውን አስታወቁ። ሰዓቱን ስንመለከት 11፡30 ይላል። ጊዜው እየመሸ በመሄዱ «እባካችሁ እዚህ ማደር አለብን፤ ካልሆነ እኛን አውርዱን!» ብለን ብንማጸንም ሰሚ አጣን።

በዚህ ጊዜ ተሳፋሪዎች በሙሉ ከተቀመጡበት ተነስተው «በህግ! በህግ» እያሉ መጮህ ጀመሩ። አንዳንዶችም ከሾፌሩና ከረዳቱ ጋር

ለድብድብ እየተጋበዙ ወደ ፊት ለፊት ሄዱ። ከዚህ ግርግር በኋላ ሾፌሩ አውቶቡሱን ያዝ አድርጎ «መውረድ የምትፈለጉ ትኬቱን መልሱና ውረዱ፤ ቀሪ ሂሳባችሁን ተሳስብን እንመልስላችኋለን» አለ፤ ቀጠል አድርጎም «እኔ ከአዲስ አበባ ወደ ቴፒ ስመጣ የመንጃ ፍቃዴን ባለመያዜ ተከስሻለሁ። ዛሬ ከዚህ ሄጄ አዲስ አበባ በመግባት ጧት ተነስቼ ስራ መስራት አለብኝ። እናም የተቀጣሁትን ገንዘብ ሰርቼ መክፈል ስለምፈልግ የመጣው ቢመጣ እዚህ አልቀርም» ብሎ የአውቶቡሱን ሞተር አሟሙቆ በረራውን ቀጠለ።

እኛም የምናደርገውን ነገር ስላጣን በታወከ ልብና በተረበሸ መንፈስ ጉዟችንን ወደ አዲስ አበባ ቀጠልን። ሾፌሩም በፍጥነት ላይ ፍጥነት እየጨመረ 2፡30 ካለፈ በኋላ አዲስ አበባ መናኸሪያ ይዞን ገባ። እኛም ከአውቶቡሱ ከወረድን በኋላ ወዴት እንደምንሄድ፣ የት እራት እንደምናገኝና የት እንደምናድር ግራ ተጋብተን ለጥቂት ደቂቃ ቆምን። ከዚያም ቀደም ሲል አዲስ አበባ ስንመጣ እናድርበት ወደነበረው እንግዳቤት ስልክ ደውለን አልጋ እንዳለ ጠየቅን። እነሱም አንድም አልጋ እንደሌለ ነገሩን።

«ምነው ፈጣሪ! እንዴት እዚህ በዘራፊዎች እጅ እንድንወድቅ አደረግህ?» ብለን በፈጣሪ ላይ ማጉረምረም ጀመርን። መፍትሔ ስናጣ ክፍለ ሀገር ወዳሉ ሰዎች ስልክ ደውለን ያለንበትን ሁኔታ ለአንዱ ወዳጃችን ነገርን። በስልክ ያገኘነው ሰው አቶ ተስፋይ አይኖ ነበር። እሱ ብዙ ከተጨነቀ በኋላ ወደ ደንበኞቹ ስልክ ደውሎ ለእኔ እና ለጓደኛዬ አልጋ አገኘልን። ይሁንና አልጋው የሚገኝበትን አቅጣጫ ስላልነገረን

እንደገና ስልክ ደወልን። በተነገረን አቅጣጫ መሰረት በእግራችን 30 ደቂቃ ከሄድን በኋላ የተባለው ቦታ ደረስን።

እንግዳቤቱ ስንደርስ በሩ ተዘግቶ ነበርና መግቢያውን አንኳኳን። ዘበኛውም «ማነው? ከዬት ነው የመጣችሁት?» ብሎ ጠየቀን። እኛም ፈጠን ብለን «ከክፍል ሃገር ነው የመጣነው፤ እዚህ አልጋ ተይዞልናል» አልን። እሱም «እስኪ አንድ ጊዜ እዚያው ቆዩ» ብሎን ወደ ውስጥ ገባ አለና የእንግዳ አስተናጋጆቹን ጠይቆ ተመለሰ። እውነትም አልጋ የተያዘልን መሆኑን ስላረጋገጠ በሩን ከፍቶ እንድንገባ ፈቀደልን። እኛም ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ዘልቀን መታወቂያችንን አሳይተን ከተመዘገብን በኋላ በየስማችን ወደተያዘልን ክፍል ገባን።

ሻንጣችንን አስቀምጠን ትንሽ አረፍ ካለን በኋላ ምሳም ሆነ እራት እንዳልቀመስን ለእንግዳቤቱ ጥበቃ በማስረዳት ወጣ ብለን ምግብ በልተን እንድንመለስ ጠየቅነው። እሱም ሁኔታችንን አይቶ የተረዳ ይመስላል፤ እናም ውጭ ለመውጣት ሰዓት እንዳለፈ ከገለጸልን በኋላ «ጥቂት ደቂቃ ተጠቀማችሁ፥ ቶሎ ተመለሱ» አለን። እኛም ፈጠን ብለን ወጣንና እራት ማጠያየቅ ጀመርን። የሁሉም መልስ «የለም! ምንም የለም!» የሚል ሆነ። በመጨረሻም ከመንደሩ ዋና መንገድ ትንሽ ወደ ውስጥ ገባ ብለን አንድ ትንሽ ምግብ ቤት አገኘንና ገባን። ያገኘነው እንጀራም ሆነ ወጥ በጣም የቀዘቀዘ ነበር። ምንም ይሁን ምን፤ በጣም ስለራበን የቀረበልንን ጥርግ አድርገን በልተን ወደ ማደሪያችን ተመልሰን።

መብራቴ ኃይሌ

# የቲኬቱ መዘዝ


ግንቦት 4/2006 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚካሄደው የመሰረተ ትምህርት አስተባባሪዎች አውደ ጥናት ላይ እንድካፈል የተነገረኝ ሚያዝያ 25/2006 ዓ.ም. ነው። መልእክቱንም የነገሩኝ በሸኪቾ የመጽሃፍ ቅዱስ ትርጉም አስተባባሪ የሆኑት ቄስ ተስፋዬ አይኖ ነበሩ።

እኔም ሚያዚያ 26/2006 ዓ.ም. ልብሴን አጣጥቤ ለጉዞዬ የሚሆን ነገር ሁሉ አሰናዳሁ። ግንቦት 01/2006 ዓ.ም. ከምኖርበት ከሸካ ዞን ከማሻ ከተማ ከማለዳው 11፡30 ሰዓት ላይ ቤተሰቦቼን ተሰናብቼ ወደ የኪ ወረዳ ቴፒ ከተማ አመራሁ። 5፡30 ሲሆን ቴፒ ከተማ ደረስኩ። ቴፒ እንደደረስኩ ቁርሴን ከጓደኛዬ ጋር በላሁ። ከዚያም ጥዋት ወደ አዲስ አበባ የምጓዝበትን የአውቶቡስ ቲኬት መግዛት አሰብኩ። ይሁንና አስቀድሜ ሻንጣዬን ማስቀመጥ ስለነበረብኝ አልጋ ለመያዝ ወደ ኃይሌ መለኮት ብርሃኔ ፀጋዬ ሆቴል ጎራ አልኩ። የሆቴሏን አልጋ አከራይ «አልጋ አለ?» ስል ጠየኳት። እሷም ከተነጠፉት አልጋዎች መካከል አንዱን በ50 ብር አከራይታኝ ሻንጣዬን አስቀምጬ ወደ አውቶቡስ ተራ አመራሁ።

ወደ አዲስ አበባ የምሄድበትን የአውቶቡስ ቲኬት በ218 ብር ከ85 ሳንቲም ቆረጥኩ። አሁን ጉዞዬ መሳካቱ እየተሰማኝ ነው። ትኬቴን በኪሴ ከትቼ ከተማዋን ከጓደኛዬ ጋር እየተዘዋወርኩ ስቃኝ ሳላስበው የምሳ ሰዓት ደረሰና ከዚሁ ጓደኛዬ ጋር ምሳዬን በላሁ። ከዚያም በቴፒና ፍሬዋ ካፍቴሪያ ሻይ ቡና እያልን ስንጨዋወት ጀንበሯ ጠለቀች። ብዙ ሳይጨልም ከጓደኛዬ ጋር እራቴን በልቼ ወደ መኝታዬ አመራሁ።

መኝታ ክፍሌ እንደገባሁ ስለ ነገው ጉዞዬ ፀሎቴን አደረስኩ። ከዚያም በማለዳ 11፡30 ላይ መንቃት እንድችል ሞባይሌን ሞላሁና ተኛሁ።

ሞባይሌ በሞላሁት መሰረት የማንቂያ ደውሉን ሲያሰማኝ ለጸሎት ተነሳሁ። የማለዳ ጸሎቴን ካደረስኩ በኋላ ወደ መናኸሪያ ለመሄድ በሬን ከፍቼ ወጣሁ። ከእኔ በፊት ከሆቴሉ የወጣ ሰው አልነበረም መሰለኝ የግቢው በር አልተከፈተም ነበር። ስለዚህ የጥበቃ ሰራተኛው የግቢውን በር ከፍቶ እንዲያስወጣኝ የተኛበትን ክፍል አንኳኳሁ። ሰራተኛውም ተነሳና በሩን ከፍቶ አስናበተኝ። ከዚያም ወደ አውቶቡስ ተራ ጉዞዬን ቀጠልኩ። መናኸሪያ እንደደረስኩ በትኬቱ ላይ የሰፈረውን የአውቶብስ የጎን ቁጥር አወጣሁና የምሳፈርበትን አውቶብስ ፈልጌ አገኘሁ። አውቶብሱ ውስጥ ከገባሁ በኋላ በወንበር ቁጥር 23 ላይ አረፍ ብዬ አምላኬ ጉዞዬን እንዲያቀናልኝ ተማፀንኩት።



መንገደኞችም ስፍራ ስፍራቸውን እየያዙ ነው አንድ አባት ግን ትክክለኛ የመቀመጫ ቦታቸውን አጥተው ከተሳፋሪዎች ጋር እየተጨቃጨቁ ነበር። አንድ ቦታ ሲቀመጡ አንዱ የእኔ ነው ብሎ ያስነሳቸዋል፤ ያንን ለቀው ሌላ ቦታ ሲቀመጡ ደግሞ ሌላው መጥቶ

ያስለቅቃቸዋል። በመጨረሻም በጣም ተበሳጭተው አንድ ቦታ ላይ ቁጭ አሉ። አፍታም ሳይቆዩ መቀመጫው ላይ መቀመጥ ያለበት ሰው መጣ። ሰውየውም እንደሌሎቹ ተሳፋሪዎች አላመነጫጨቃቸውም። ይልቁንም ተረጋግቶ «አባቴ ቲኬትዎ የት አለ?» ብሎ ጠየቃቸው። እሳቸውም ከኪሳቸው መዘዝ አድርገው አሳዩ። ትኬቱ ሲታይ የወንበር ቁጥር አልተፃፈበትም። በኋላም ተሳፋሪዎቹ ጥፋቱ የሽማግሌው ሳይሆን የቲኬት ቆራጩ መሆኑን ስለተረዱ መቀመጥ ያለባቸውን ቦታ በጋራ ከለዩ በኋላ ተረጋግተው እንዲቀመጡ አደረጓቸው። ጭቅጭቁም ትርምሱም ቆመና ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ ጉዟችንን ጀመርን።


የሸካን ዞን ጨርሰን ወደ ካፋ ዞን ገባን። ካፋ ዞን ቦንጋ ከተማ እንደደረስን ለቁርስ ወረድን። ከጓደኛዬ ጋር ቢትኖ ሆቴል ገባንና ቁርሳችንን በላን። ከዚያም ትኩስ ነገር ፈለግንና ሻይ ቡና ለማለት ከሆቴሉ ፊት ለፊት ካለው ካፌ ገባን። ሻይ ቡና ካልን በኋላ ወደ አውቶቡሱ ገብተን ተቀመጥን። አውቶቡሱም መብረሩን ቀጥሎ ልክ 6፡30 አካባቢ ጂማ ደረስን። ጂማ ላይ ምሳ እንድንበላ ሁላችንም ጥያቄ አቀረብን፡፡ ሾፌሩና ረዳቱ ግን ተማከሩና «በጊዜ ወልቂጤ ገብተን እንድናድር ጉዟችንን መቀጠል አለብን። አዚያው ስትደርሱ ትበላላችሁ» ብለው ምሳችንን እንዳንበላ ማእቀብ ጣሉብን። ምንም ማድረግ ስላልቻልን በባዶ ሆዳችን ጉዟችንን ተያያዝነው። እንደ ምንም ጥርሳችንን ነክሰን ጊቤ ደረስን። ከጊቤ ቆሎ ገዝቼ ከጓደኛዬ ጋር እየቆረጠምኩ ወልቂጤ ደረስን።

ሾፌሩና ረዳቱ በገቡልን ቃል መሰረት ወልቂጤ ያሳርፉናል ብለን በደስታ «እሰይ! አሁን ልናርፍ ነው» ብለን ተሳፋሪዎች በሙሉ ሻንጣችንን እና እቃችንን ማስተካከል ጀመርን። ሾፌሩ ግን «አዲስ አበባ ገብተን ስለምናድር፥ አትውረዱ» ብሎ ፍጥነቱን ጨመረ።

በአውቶብሱ ያለን ተሳፋሪዎች በሙሉ ከተቀመጥንበት ተነስተን «በሕግ! በሕግ አምላክ! አቁም! አውርደን» እያልን ብንጮህ፣ ብንማፀን ሰሚ አጣን።

ሾፌሩ ከአዲስ አበባ ወደ ቴፒ ሲሄድ ትርፍ በመጫኑ ምክንያት ቅጣት ተቀጥቶ ነበር። ስለዚህ አዲስ አበባ አምሽቶም ቢሆን ከገባ በኋላ በማግስቱ እየሰራ በመዋል በቅጣት የተወሰደበትን ብር ለማካካስ አስቧል። ለዚህም ነው ዳጋግመን «በሕግ» እያልን ያቀረብነውን ተማጽኖ ለመስማት ፈቃደኛ ያልነበረው። በዚህም ይሁን በሌላ ምክንያት ሳንወድ የምሽት ጉዟችንን ተያያዝነው። ልክ ከምሽቱ 3፡30 አካባቢ ነበር አውቶቡስ ተራ የደርሰነው። በዚያ ምሽት ማረፊያ ፍለጋ እኔና ጓደኛዬ ወደ ጉላሌ ቤቴል ሲኖዶስ እንግዳ ማረፊያ አመራን። ጉዟችንም በዚህ መልኩ ተጠናቀቀ።

አዲስዓለም ኃይሌ




www.idp-uk.org/Resources/Maps/EthiopiaRegions.gif